# በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ማዕ/ጎ/ሀ/ስ ለደብረ ኀይል ወደብረ ጥበብ በአታ ለማርያም ካቴድራል የተሰጠ

# የነገረ አበው ኮርስ




አዘጋጅ፡- በትረማርያም አበባው ካሣ

(የመጻሕፍተ ብሉያት፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)


ሐምሌ ፩፣ ፳፻፲፫ ዓ.ም

# ነገረ አበው (Patrology)

የቀድሞ ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ሊቃውንትና ወደፊትም እስከ ዕለተ ምጽአት የሚነሡ የእግዚአብሔርን ሕግ ጠብቀው ያስጠበቁና የሚያስጠብቁ ቅዱሳን አበው ይባላሉ፡፡ ነገረ አበው የቀደምት አበውን ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮና የሕይወት ቅድስና የምናጠናበት የትምህርት ክፍል ነው፡፡ ነገረ አበው እንደ አንድ የነገረ መለኮት ትምህርት ክፍል የሚጠና ብቻ ሳይሆን በሁሉም የነገረ መለኮት ትምህርት ክፍሎች የሚገኝ ትምህርት ነው፡፡ ነገረ አበው ከሐዋርያት በኋላ የተነሡና በጽሑፍና በቃል የተሰጣቸውን ታላቁን ሐዋርያዊ ትውፊት ጠብቀው ከከሓድያን እየተከላከሉ ያስተላለፉ፣ መጻሕፍትን የተረጎሙ፣ ድርሳናትን የደረሱና በአጠቃላይ በሕይወታቸውም በትምህርታቸውም ቤተክርስቲያን የመሰከረችላቸው አበው የሚወሱበት የነገረ መለኮት ትምህርት ዘርፍ ነው፡፡ ነገረ አበው የቤተክርስቲያን አባቶች ሕይወታቸው እና ትምህርታቸው የሚጠናበት የነገረ ትምህርት ክፍል ነው፡፡ በጥንታዊት ቤተክርስቲያን ታሪክ ነው፡፡ በጥንታዊት ቤተክርስቲያን ታሪክ የሚታወቁ አባቶችን ታሪክ ማወቅ ስለጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን አምልኮት፣ ማኅበራዊ ሕይወትና አጠቃላይ የመንፈሳዊ ሕይወት ታሪክ በቀላሉ ለመረዳት ያስችላል፡፡ የቤተክርስቲያን አባቶች ቤተክርስቲያን አንድነቷ ጸንቶ እንዲኖር በረቂቅ ለሚጠብቃት መንፈስ ቅዱስ በሚታይ ገንዘብ ጠባቂዎች ናቸው፡፡

## የነገረ አበው አስፈላጊነት

ቤተክርስቲያን ትምህርቷንና ሕይወቷን ከትውልድ ወደ ትውልድ የምታስተላልፍበት ሕያው መንገዷ በየዘመኑ የሚነሡ በሕይወታቸውም በትምህርታቸውም የወንጌልን ሕይወት የኖሩና ሌሎችም ይቀበሉት ዘንድ ባስተማሩ ቅዱሳን ነው፡፡ የቤተክርስቲያን ትምህርቷና ሕይወቷ በቅድስና በኖሩና የመጻሕፍትን ምስጢር በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በተረዱ ቅዱሳን ሰዎች በኩል የሚተላለፍ እንጂ በቅዱሳት መጻሕፍት ንባብ ብቻ የሚተላለፍ አይደለም፡፡ ነገረ አበው የሚከተሉት ጥቅሞች አሉት፡፡

- ቅዱሳት መጻሕፍትን በትክክል ለመረዳት
- ነገረ ቤተክርስቲያንን (አሠራሯን፣ ሥርዓተ አምልኮዋን፣ መሥዋዕቷን…ወዘተ ለመረዳት፡፡ ቤተክርስቲያን በምድርም ያለች የእግዚአብሔር መንግሥት ናትና)
- የቤተክርስቲያንን ታሪክ ለመረዳት (ነገረ አበው የታሪካዊ ነገረ መለኮት ዘርፍ እንደመሆኑ የቤተክርስቲያንን ታሪክ ያለአባቶች ለማወቅ መሞከር ከቶ አይቻልምና)
- ክርስቲያናዊ ኑሮን ለመረዳት (ክርስቲያኖች እንዴት እንደኖሩና እንዴት መኖር እንዳለባቸው ያሳውቀናል)
- ነገረ ማርያምን፣ ክርስቲያናዊ ምግባርን፣ ነገረ ክርስቶስን፣ ነገረ ቅዱሳንንና የመሳሰሉትን በትክክል ለመረዳት

ኦርቶዶክሳዊውን አስተምህሮ በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር ያስተማሩትን የቤተክርስቲያን አባቶች እንላቸዋለን፡፡ ቅዱሳን አባቶች በኦርቶዶክሳዊው አስተምህሮ አንድ ቢሆኑም በኖሩባቸው ዘመናት፣ ቦታዎች፣ ባህሎች፣ በጊዜው የደረሱባቸው የዓለም ዕውቀቶችና ፍልስፍናዎች የተለያዩ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ እግዚአብሔር ያመላከታቸውን እውነትና እነርሱም ከደረሱበት የዕውቀት ደረጃ አንጻር አንዳንድ ጉዳዮችን በሚገልጹበት መንገድ የተለያዩ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ይህም የአገላለጽ (Way of expression) ነው እንጂ የአስተምህሮ ልዩነት አይደለም፡፡

## የቤተክርስቲያን አባቶችን መጻሕፍት ለመረዳት የሚያስፈልጉን ነገሮች

- የቤተክርስቲያንን ትምህርት በአንድ አባት ጽሑፍ ላይ ብቻ መወሰን አይገባም፡፡ በአንድ ርእሰ ጉዳይ ላይ በቂ ዕውቀት ለማግኘት በርከት ያሉ የአበው መጻሕፍትን መመርመር ይገባል፡፡
- ከአንድ አባት የመጽሐፍ ገጾች ከመጥቀሳችን በፊት መጻሕፍቱን አንብበን የዚህን አባት ጠቅላላ እሳቤዎች ማጥናት አለብን፡፡
- ብዙዎች አባቶች በዘመናቸው የነበሩ ፍልስፍናዎችን የተማሩ ስለነበሩ ለዘመናቸው ሰው ለማብራራት የዘመኑን የፍልስፍና ቃላት በጽሑፎቻቸው ውስጥ ተጠቅመዋል፡፡ ስለዚህ ያለፉበትን የፍልስፍና ታሪክና የዘመናቸውን የዕውቀት ክበብ ማጥናት መጻሕፍቶቻቸውን ያለጉድለት ለመተርጎምና ለመረዳት ጠቃሚ ነው፡፡
- አንድን አባት ከኖረበት ዘመን ለይቶ መመልከት አይገባም፡፡ ስለሆነም በዘመኑ የነበረውን ሃይማኖታዊ ሁኔታ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡
- ነገረ ሃይማኖታዊ ቃላትንና መግለጫዎችን እንደጊዜ ግብራው መመልከት፡፡
- ከአንድ አባት የተጠቀሰውን ቃል በዘመኑ ከነበሩ ከሌሎች አበው ጋር ማስተያየት (ማነጻጸር) ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ አበው ያስተማሩት በዋነኛነት ለዘመናቸው ትውልድ ስለሆነ የኖሩበትን ትውልድ ሁኔታ፣ ቋንቋውን፣ አስተሳሰቡን፣ አኗኗሩን፣ ባህሉንና የመሳሰሉትን ማወቅ ትምህርታቸውን በደንብ ለመረዳት ይጠቅመናል፡፡ ነገረ አበው የአበውን ታሪክ በቦታ፣ በቋንቋ፣ በዘመንና በትምህርታቸው ከፋፍሎ አደራጅቶ የሚያሳውቀን ትምህርት ነው፡፡

## የቤተክርስቲያን አባቶች መመዘኛ መስፈርቶች

የማንኛውም ሰው ትምህርት መመዘኛ ቅዱሳት መጻሕፍትና ቅዱስ ትውፊት ናቸው፡፡ ስለዚህ የአንድ አባት ተጠቃሽነት ከሁለቱ ጋር እስከተስማማ ድረስ ነው፡፡ አንድ አባት የቤተክርስቲያን አባት ለመባል ቢያንስ የሚከተሉት መስፈርቶች ሊኖሩት ይገባል፡፡

- ኦርቶዶክሳዊ ድርሳናትን የጻፈ
- ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ ያለው
- የሕይወት ቅድስና ያለው
- ቀደምትነት ያለው

ምንም እንኳ አበው ከአዳም ጀምሮ እስከ ዕለተ ምጽአት የሚነሡ ቢሆንም በነገረ መለኮት ምሁራን ግን ከአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያሉ አባቶችን ታሪክና ትምህርት በተለየ የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ ነው፡፡ በእነዚህ ዘመናት የተነሡ አበው በዋናነት የሚከተሉትን ሥራዎች ሠርተዋል፡፡

- ✓ በሥርዓተ ቤተክርስቲያን ዙሪያ መጻሕፍትን ጽፈዋል፡፡
- ✓ በየዘመናቱ ለተነሡ ከሓድያን ምላሽ በማዘጋጀት የጥብቅና (Apologetics) ሥራ ሠርተዋል፡፡
- ✓ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አረዳዱ እንዳይበረዝ ከቀድሞ ጀምሮ የነበረውን ትርጉም ገልጸው ጽፈዋል፡፡

- ✓ ከአይሁድ፣ ከፈላስፎች፣ ከከሓድያን፣ ከዐላውያን ነገሥታት በቤተክርስቲያን ላይ የሚደርሰውን መከራ ፊት ለፊት በመጋፈጥና ሰማዕት እስከመሆን በመድረስ ትክክለኛውን ትምህርት አስተላልፈዋል፡፡
- ✓ መጽሐፍ ቅዱስ ተርጉመዋል፡፡
- ✓ ሥርዓተ መነኰሳትን ሠርተዋል አስፋፍተዋል፡፡

## የነገረ አበው ክፍሎች

ነገረ አበው በልዩ ልዩ የአከፋፈል መንገዶች ይጠናል፡፡ ይህም ዘመንን መሠረት በማድረግ፣ ቦታን መሠረት በማድረግ፣ ትምህርትን መሠረት በማድረግ፣ ቋንቋን መሠረት በማድረግና በመሳሰሉት መንገዶች በመከፋፈል ይሰጣል፡፡

## ዘመንን መሠረት ያደረገ የነገረ አበው ትምህርት አከፋፈል

- ሐዋርያውያን አበው፡- ይህ ከአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ ሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ አባቶች ሕይወትና ትምህርት የሚጠናበት ነው፡፡ በዚህ ዘመን ከሚጠቀሱ አባቶች መካከል አግናጥዮስ ዘአንጾኪያ፣ ቅዱስ ፖሊካርፐስ፣ ቀሌምንጦስ ዘሮም ይጠቀሳሉ
- ቅድመ ኒቅያ የነበሩ አበው፡- ይህ ዘመን ከሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ 325 ዓ.ም የነበሩ አበው ሕይወትና ትምህርት የሚጠናበት ነው፡፡ በዚህ ዘመን ከሚጠቀሱ አባቶች መካከል ቅዱስ ሄሬኔዎስ ይጠቀሳል፡፡
- ጊዜ ኒቅያና ድኅረ ኒቅያ የነበሩ አበው፡- ይህ ዘመን ከ325 ዓ.ም እስከ 430 ዓ.ም ማለትም እስከ ጉባኤ ኤፌሶን በነበረው ዘመን የተነሡ አባቶች ሕይወትና ትምህርት የሚጠናበት ነው፡፡ በዚህ ዘመን ከተነሡ አባቶች መካከል ቅዱስ አትናቴዎስ፣ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያና ሌሎችም ቅዱሳን ሊቃውንት ተነሥተዋል፡፡
- የኋላ ዘመን አበው፡- ይህ ዘመን ከ430 ዓ.ም እስከ 850 ዓ.ም የነበሩ ቅዱሳን አበውን ሕይወትና ትምህርት የምናጠናበት ዘመን ነው፡፡ በዚህ ዘመን እነ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ፣ ቅዱስ ያሬድ፣ ተስዓቱ ቅዱሳንና ሌሎች አባቶች ይጠቀሳሉ፡፡

## ቦታን መሠረት ያደረገ የነገረ አበው አከፋፈል

- ➢ የእስክንድርያ አባቶች፡- በምስጢራዊ የትርጓሜ ስልት (Allegorical interpretation) ይታወቃሉ፡፡ በዚህ የትርጓሜ ስልት ከሚጠቀሱ አባቶች መካከል ቅዱስ ቄርሎስ ይጠቀሳል፡፡
- ➢ የአንጾኪያ አባቶች፡- በቃላዊና በዐውዳዊ ትርጓሜ ስልት (Literal interpretation) ይታወቃሉ፡፡ በዚህ ከሚታወቁ አበው መካከል ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይጠቀሳል፡፡

በነገረ አበው ጥናት የቀጰዶቅያ አባቶች ተብለው የሚጠሩት ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙና ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ናቸው፡፡ ቋንቋን መሠረት ባደረገ አከፋፈል የግሪክ ቋንቋ፣ የሶርያ ቋንቋና ሌሎች ቋንቋዎች ተብሎ ይከፈላል፡፡

## አበውና ትምህርቶቻቸው

**፩. ቅዱስ አግናጥዮስ፡-** ከ30-35 ዓ.ም ባለው ዘመን ተወለደ፡፡

- ቴኦፎሮስ (ለባሴ እግዚአብሔር) በመባል ይታወቃል፡፡
- የዮሐንስ ወንጌላዊ ደቀመዝሙር የነበረ ነው፡፡

- ጌታ ለሐዋርያት ትሕትናን ያስተማረበት ሕፃን ነው።
- በትራጃን ቄሣር ዘመነ መንግሥት ለአንበሶች ተጥሎ ሰማዕትነቱን የፈጸመ በመሆኑ ምጥው ለአንበሳ እየተባለም ይጠራል።
- በነገረ ሥላሴ ዙሪያ እግዚአብሔር በአካል ሦስት፣ በባሕርይ አንድ መሆኑንና ባሕርይ ማለትም የሦስቱ አካላት መገናዘብ እንደሆነ አስተምሯል። ባሕርይን "ዘውእቱ አሐዱ ብርሃን ዘይሠርቅ እምኔሁ ሥላሴ-ከእርሱ ሦስትነት የሚገኝ አንድ ብርሃን ነው። አንድም ዘይሠርቅ እምኔሁ ለሥላሴ-ከሦስትነት የሚገኝ አንድ ብርሃን ነው" በማለት ገልጾታል (ሃይ.አበ.11፥19)።
- በነገረ ሥጋዌ ዙሪያ ደግሞ ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ በተለየ አካሉ በተለየ ከዊኑ ሰው መሆኑን ለመግለጽ "በእንተ ተዋሕዶተ መለኮት ዘንትናገር በዝየ ዘህልው በወልድ ወአኮ በእንተ አብ ወመንፈስ ቅዱስ" ብሎ ገልጾልናል (ሃይ.አበ.11፥3)።
- ክርስቶስን ምትሐት፣ ኅድረት ለሚሉ ከሓድያን ምላሽ የሚሆን ትምህርትም "አማን ተወልደ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ። እሙነ ልህቀ፣ እሙነ በልዐ ወሰትየ፣ እሙነ ተሰቅለ፣ ወእሙነ ሐመ ወሞተ ወተቀብረ ወተንሥአ እሙታን" በማለት አስተምሯል (ሃይ.አበ.12፥2)። ለሥጋ በነፍሱ ምትክ መለኮቱ ሆነው ለሚሉትም ተከዘት ነፍስየ እስከ ለሞት የሚለውን የወንጌል ቃል በመጥቀስ ለክርስቶስ ስበኣዊት ነፍስም እንዳለችው ገልጿል (ሃይ.አበ.11፥16)።
- ክርስቶስን ሞተ ባልነው ጊዜ በሥጋው እንጂ በመለኮቱ እንዳልሆነ ለመግለጽ "ኢተአምርኑ ለእመ ትቤ ከመ መለኮት ሞተ አንተ ትከውን ቀታሊሆሙ ለሥሉስ ቅዱስ። መለኮት ሞተ ካልክ የሥላሴ ገዳይ እንደሆንክ አታውቅምን በማለት አስተምሯል (ሃይ.አበ.11፥13)።

**፪. ቅዱስ ዲዮናስዮስ ዘአርዮስ ፋጎስ፡-** በግሪክ አቴንስ የፍልስፍና መምህር የነበረ ነው።

- ❖ ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ፀሐይ በዓለም ሁሉ ጨልማ ስለነበር ያንን በብረት ሰሌዳ ጽፎት ነበር። በኋላ ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስተምር ሰምቶ አምኗል።
- ❖ ይህንን ዓለም ካለመኖር ወደመኖር ያመጡት ሥላሴ እንደሆኑ ተናግሯል (ሃይ.አበ.10፥7) የወልድ ከአብ መወለድና የመንፈስ ቅዱስ መውጣት ይደነቃል እንጂ አይነገርም ያለ ሊቅ ነው (ሃይ.አበ.10፥12-13)።

**፫. ቅዱስ ፖሊካርፐስ፡-** ይህ አባት በ69 ዓ.ም ተወልዷል። በ155 ዓ.ም አርፏል። የወንጌላዊው የቅዱስ ዮሐንስ ደቀመዝሙር የነበረ ነው።

**፬. ቅዱስ ሄሬኔዎስ፡-** በ125 ዓ.ም ተወለደ። በ202 ዓ.ም አረፈ። ይህ አባት በተለይ በዕቅበተ እምነት ብዙ የሠራ አባት ነው። ቤተክርስቲያንን ከግኖስቲኮች ትምህርት የጠበቀና የግኖስቲኮችን ትምህርት በመቃወም ይታወቃል። የቅዱስ ፖሊካርፐስ ደቀመዝሙር ነው። ለመናፍቃን መልስ የጻፈው መጽሐፍ (Against Heresies) ታዋቂ ነው። ከትምህሮቹ መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ

- ○ ኦሪትም፣ ነቢያትም፣ ወንጌልም ክርስቶስን እንዳስተማሩ ገልጿል (ሃይ.አበ.7፥2)
- ○ መጻሕፍት ስለክርስቶስ ሲናገሩ አንዳንድ ጊዜ ስለሰውነቱ አንዳንድ ጊዜ ስለአምላክነቱ ቢናገሩም አንድ አምላክ መሆኑን "በከመ ይነግራነ መጻሕፍት ቅዱሳት ከመ ክርስቶስ ሰብእ ከማሁ ይነግራነ ከመ ውእቱ አምላክ። ወበከመ ያየድዓነ ከመ ውእቱ ሥጋ ከማሁ ያየድዓነ ከመ ውእቱ መንፈስ" በማለት አስተምሯል (ሃይ.አበ.7፥19)።

**፭. ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት፡-** በ213 ዓ.ም ተወለደ፡፡ ጎርጎርዮስ ማለት ዕቁብ (የተጠበቀ)፣ ንቁህ (የነቃ) ማለት ነው፡፡

- አካላዊ ቃል ወልደ እግዚአብሔር ከዝርዋን ቃላት እንደሚለይ ለመግለጽ "ወለዝንቱ ስም ዘውእቱ ቃል ንሌብዎ እምሠለስቱ ቃላት፡፡ ወአኮ እሙንቱ ህልዋን በአካላት፡፡ አተርጋዎን አኮ ውእቱ ሀላዊ በአካል፡፡ ወቦርፎሪኮንኒ ውእቱ ቃል ዘሰምዕዎ ነቢያት እምኀበ እግዚአብሔር፡፡ አአትሪኮን ውእቱ ቃልነ ዘይትከዐው ውስተ አየር ወአኮ ውእቱ ሀላዊ በአካል" ብሏል (ሃይ.አበ.13፥22)፡፡
- አተርጋዎን የመላእክት ቃል ነው፡፡ ቦርፎሪኮን ነቢያት ከእግዚአብሔር የሰሙት ቃል ነው፡፡ አአትሪኮን የሰው ቃል ነው፡፡ እነዚህ ሦስቱም ቃላት ዝርዋን ቃላት ናቸው፡፡

**፮. ቅዱስ እለእስክንድሮስ፡-** በ250 ዓ.ም ተወለደ፡፡ በ328 ዓ.ም አርፏል፡፡ የተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ ደቀመዝሙር የነበረና የኒቅያ ጉባኤ አፈ ጉባኤ የነበረ ነው፡፡ ይህ ቅዱስ የወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆን እኛን ለመጥቀምና ለእኛ መሆኑን ለመግለጽ "ምንትኑ አጽሐቆ ይረድ እግዚአብሔር ቃል ውስተ ምድር ወይሠገው እምቅድስተ ድንግል ወይጠብለል በአጽርቅት ወይትወደይ ውስተ ጎል…አኮኑ ውእቱ በእንቲኣነ ለነ ለእለ ማሰነ" ብሏል (ሃይ.አበ.16፥3)፡፡

**፯. ቅዱስ አትናቴዎስ፡-** በ298 ዓ.ም በእስክንድርያ ተወለደ፡፡ ከቅዱስ እለእስክንድሮስ የቤተክርስቲያንን ትምህርት ተማረ፡፡ ወልድ በመለኮቱ ፍጡር ያለ አርዮስን ከ318ቱ ቅዱሳን ሊቃውንት ጋር ሆኖ የረታ ሊቅ ነው፡፡ በአርዮሳውያን ሴራ አራት ጊዜ ከመንበሩ የተሰደደና ብዙ መከራን የተቀበለ አባት ነው፡፡ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ አትናቴዎስ የቤተክርስቲያን ዐምድ እያለ ይጠራው ነበር፡፡ ቅዱስ አትናቴዎስ ከጻፋቸው መጻሕፍት መካከል ገድለ እንጦንስ፣ በእንተ ስደት፣ በእንተ ሥጋዌ (On the incarnation) እና አርዮሳውያንን በመቃወም የጻፈው (Against Arians) ይጠቀሳሉ፡፡ ይህ ቅዱስ ሥጋ በተዋሕዶተ ቃል እንደነበረ ለመግለጽ "ሥጋ ረከበ ዕበየ ወብዝኀ ፍድፍና በተሳትፎቱ ወበተዋሕዶቱ ምስለ ቃል" ብሏል (ሃይ.አበ.31፥18)፡፡ አትናቴዎስ ያረፈ ግንቦት 7 ቀን በ373 ዓ.ም ነው፡፡

**፰. ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ፡-** በ330 ዓ.ም ተወለደ፡፡ አባቱም ባስልዮስ ይባላል፡፡ ማክሪና የምትባል ደግ እኅትም ነበረችው፡፡ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ወንድሙ ነው፡፡ በትምህርቱ ብስለት ምክንያት ታላቁ ባስልዮስ እየተባለ ይጠራል፡፡ ከነገረ መለኮት በተጨማሪ የሕግና የንግግር ክሂሎትን ተምሯል፡፡ በየገዳማቱ ተዟዙሮ ያያቸውን የምንኵስና ሥርዓቶች በአካባቢው አስፋፍቷል፡፡ ጸሎተ ቅዳሴን፣ አክሲማሮስን፣ በእንተ መንፈስ ቅዱስንና ሌሎች መጻሕፍትን ጽፏል፡፡ ገዳማዊ ሕይወትን የተመለከቱ ጽሑፎችንም ጽፏል፡፡ እግዚአብሔር በኀሊና ከመመርመር በላይ መሆኑን ለመግለጽ "ቦኑ ይትከሀለነ ንጠይቅ ስፍሐ ሰማይ ወዕመቀ ቀላይ፡፡ እስመ ኢንክል ንጠይቅ ኀዳጠ እምፍጡራን እፎኑመ ይትከሀለነ ንብጻሕ ኀበ አእምሮተ እግዚአብሔር፡፡ ወንኅድግ ኵሎ አእምሮ ለእግዚአብሔር ዘይመውዕ ኵሎ ግብራተ" ብሏል (ሃይ.አበ.33፥12)፡፡

**፱. ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ፡-** በ329 ዓ.ም ተወለደ፡፡ በ390 ዓ.ም አረፈ፡፡ በነገረ መለኮታዊ ትምህርት ጥልቅ ዕውቀት ስለነበረው ነባቤ መለኮት እየተባለ ይጠራል፡፡ ይህም ስመ ሥርጋዌ ይባላል፡፡ ናጣሊስ ማኅቶት ብሩህ፣ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቄርሎስ መምህረ ዓለም፣ ኤፍሬም አፈ በረከት እንደሚባሉት ያለ ነው፡፡ ይህ ጎርጎርዮስ ከሁሉ አስቀድሞ ምስጢረ ሥላሴን ማወቅና ማስተማር እንደሚገባ "መቅድመ ኵሉ ንሰብክ ሥላሴ ዕሩየ ወቅድስተ ዘውእቶሙ አብ ወወልድ

ወመንፈስ ቅዱስ" ብሏል (ሃይ.አበ.60፥2)። በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ የግብር፣ የስም፣ የአካል ተፋልሶ እንደሌለም አስተምሯል (ሃይ.አበ.60፥9)። ከሥላሴ ፍጡር የለም ብሏል (ሃይ.አበ.60፥6)። ድንግል ማርያም ወልደ እግዚአብሔርን ያለወንድ ዘር፣ ያለምጥ፣ ያለሕማም እንደወለደችውም አስተምሯል (ሃይ.አበ.60፥14-15)።

**፲. ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፦** በ335 ዓ.ም ተወለደ። በ395 ዓ.ም አረፈ። ድንግል ማርያም ዕረፍትህ ከዕረፍቴ ቀን ነው ብላው ጥር 21 ቀን አርፏል። ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ስለሆነ ታላላቅ ሥራዎችን ለመለኮት፣ ታናናሽ ሥራዎችን ለሥጋ እያልን መናገር እንደማይገባን "ወኢተነሊ ምግባራተ ልዑላተ ለአሐዱ ባሕቲቱ ወዘይቴሐት ለካልኡ። አላ ዝንቱ ወዝክቱ ኵሉ ለዝንቱ አሐዱ ባሕቲቱ" ብሏል (ሃይ.አበ.35፥27)። አምላክ ሰው ሰው አምላክ ሲሆን ያለመለወጥ በተዓቅቦ መሆኑን ለመግለጽም "ዝንቱ ውእቱ እግዚአብሔር ወውእቱ ብእሲ ወኢኮነ ክልኤተ። ኢያፍለሰ ፈጣሪ መለኮቶ ለከዊነ ፍጡር ወኢደምሰሰ ትስብእቶ ፍጡረ ለከዊነ ፈጣሪ" ብሏል (ሃይ.አበ.36፥24)። በክርስቶስ መከራ እኛ ክብርን እናገኝ ዘንድ ክርስቶስ መከራ መቀበሉንም "ወነድየ ከመ ንብዐል ንሕነ በንዴተ ዚኣሁ" ብሏል (ሃይ.አበ.36፥25)። ይህም ሲሆን መከራ መቀበሉ በፈቃዱ እንጂ በግድ አለመሆኑን "ዝንቱ ውእቱ ዘተወክፈ ሕማመ በፈቃዱ በሥጋሁ" ብሏል (ሃይ.አበ.36፥27)። ክርስቶስ ራሱ መሥዋዕት፣ ራሱ መሥዋዕት ተቀባይ፣ ራሱ መሥዋዕት አቅራቢ መሆኑንም "ውእቱ በግዐ መሥዋዕት ወውእቱ ካህን ሠዋዒ ወውእቱ ተወካፌ መሥዋዕት ምስለ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ" በማለት አስተምሯል (ሃይ.አበ.36፥26)።

**፲፩. ቅዱስ ኤጲፋንዮስ፦** በ310 ዓ.ም አካባቢ ተወለደ በ403 ዓ.ም አረፈ። መጽሐፈ አክሲማሮስን ጽፏል። በሃይማኖተ አበው እንደተገለጸውም ስለትንሣኤ በስፋት ጽፏል (ሃይ.አበ.58፥1፤ ሃይ.አበ.59፥1)። የቆጵሮስ ኤጲስ ቆጶስ የነበረ ነው።

**፲፪. ቅዱስ ኤፍሬም፦** ብዙ ድርሰቶችን የደረሰ አባት ሲሆን በሀገራችንም በተለየ ብዙዎቻችን የምናውቀውን ውዳሴ ማርያም የጻፈ ነው። አምላክ ሰው ሲሆን በምልአት ተዋሐደ እንጂ ከፍሎ እንዳልተዋሐደ ለመግለጽ "ወኢተዋሐደ በመንፈቀ ህላዌ" ብሏል (ሃይ.አበ.47፥32)። ድንግል ማርያም አምላክን በሥጋ እንደወለደችም "ብእሲት ምድራዊት ወለደቶ ለእግዚአብሔር ቃል ዘኮነ ሰብአ። ድንግል ወለደቶ ለገባሪሃ ወለሲሁ ፈጠረ ወላዲቶ" ብሏል (ሃይ.አበ.47፥2)።

**፲፫. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፦** በ340 ዓ.ም ተወለደ። በ400 ዓ.ም አረፈ። እናቱ በመልካም አስተዳደግ አሳድገዋለች። የቊስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት ነበረ። የፍልስፍና ትምህርትን አቴና ግሪክ ተምሯል። የቅዱስ ጳውሎስን መልእክታትና ሌሎችንም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተርጉሟል። ሲገሥጽ ማንንም አይፈራም ነበር። በግዞት ሳለ ግንቦት 12 ቀን አርፏል። ከትምህርቱ ጥራት የተነሣ አፈወርቅ፣ ልሳነ ወርቅ እየተባለ ተጠርቷል።

**፲፬. ቅዱስ ያሬድ፦** ሚያዝያ 5 ቀን በ505 ዓ.ም በአክሱም ከተማ ተወለደ። አባቱ አብዩድ እናቱ ክርስቲና ትባላለች። ብሉይ ኪዳንን ሐዲስ ኪዳንን ተምሯል። ጾመ ድጓ፣ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬ፣ መዋሥዕት የሚባሉ መጻሕፍትን ጽፏል። በእነዚህ ድርሰቶቹ ነገረ ክርስቶስን፣ ነገረ ማርያምን፣ ነገረ ቅዱሳንን፣ ሥነ ምግባርንና ሌሎችንም በሰፊው አስተምሯል። በትርጓሜ ዙሪያም ጥቂቶችን ለመመልከት ያህል "ሣህል ወርትዕ ተራከባ። ሣህልሰ ክርስቶስ ውእቱ ወርትዕሰ ዮሐንስ ውእቱ"፣ "ክልኤ አጥባቲሃ ክልኤ ሕግ ዘቤተክርስቲያን" ብሏል። ነቢዩ ኢሳይያስ ናሁ ይመጽእ እግዚአብሔር ውስተ ምድረ ግብጽ ተጽዒኖ ዲበ ደመና ቀሊል ያለውን ቅዱስ ያሬድ "ደመናሰ ዘይቤ ይእቲኬ

ድንግል ዘሐዘለቶ በዘባና ለአማኑኤል” ብሎ ተርጉሞታል፡፡ ዮሐንስ መጥምቅ ዘኢይደልወኒ እፍታሕ ቶታነ አሣዕኒሁ ያለውን ቅዱስ ያሬድ “(ዘንተ) ዘይቤ ዮሐንስ ሥጋሁ ወደሞ ለክርስቶስ” ብሎ ተርጉሞታል፡፡ ቅዱስ ዳዊት ስኖ ለያዕቆብ ዘአፍቀረ ያለውን ቅዱስ ያሬድ “ወስኑሰ ለያዕቆብ ዘይቤ ይእቲ ሥጋ እንተ ነሥአ መድኅን እማርያም” ብሎ ተርጉሞታል፡፡ የሰውን ክቡርነትና የሰንበትን ክቡርነት ለመግለጽ “ሰንበት ተዐቢ እምኵሉ ዕለት ወሰብእ ይከብር እምኵሉ ፍጥረት” ብሏል፡፡ ስለ መልካም ምግባርም “ምግባር ታበጽሕ ሰማያተ” ብሏል፡፡